## እንኳን ለብርሃነ ልደቱ አደረሳችሁ!

## እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

### ማስታወቂያ

#### የአርብ ፕሮግራም

በአርብ ፕሮግራም ዘወትር አርብ ከ7 p.m. ጀምሮ እየተገናኘን እንጸልያለን። ቃሉንም እንማራለን። በዚህ ፕሮግራም ላይ በመገኘት የበረከቱ ተካፋዮች እንድንሆን ሁላችንም እንድንሳተፍ ቤተ ክርስቲያን ታበረታታለች። በተለያየ ጉዳይ እንዲጸለይላችሁ የምትሹም አገልጋዮችን ማነጋገር ትችላላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ!

#### የሕንጻ ፈንድ ማሰባሰብ ፕሮግራም

ለሕንጻ ግዢ ለመስጠት ቃል የገባነውን ገንዘብ በገባችሁት ቃል መሰረት የፈጸማችሁ ሁሉ እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ለመስጠት ቃል የገባችሁ ደግም ስጦታውን እስከ አመቱ መጨረሻ (ወይንም ቃል በገባነው መሰረት) እንድንሰጥ እናበረታታችኋለን። የህንጻ ኮሚቴ አስተባባሪዎች።

## እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

“ወደ ውጭም አውጥቶ፦ ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው። 
እነርሱም፦ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።” (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት፦
773-886-0818 (ሲሳይ)
773-865-6102 (ብረሃኑ)
773-507-0194 (ጋሽ አያሌው)
773-910-0485 (ፒተር)
773-961-5332 (ጌቱ)

#### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

| | | |
|---|---|---|
| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |

“እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ” ሉቃስ 2፡10




“በጨለማ የተቀመጠው ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ፥ በሞት አገርና ጥላ ለተቀመጡትም ብርሃን ወጣላቸው።”
(ማቴ 4፡ 14-16)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

**January 7, 2018** | **ታኅሣስ 29፤ 2010 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................. | ወንድም ሰለሞን ወመኅ |
| አምልኮ........................ | የቤተክርስቲያን አምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ሰለሞን ወመኅ |
| ቃል ............. | እሕት መሰረት (ከኢትዮጲያ) |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### የሳምንቱ ጥቅስ

ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል። ”

*(ኢሳ. 9፡6)*

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| መሪ | ቀን | አድራሻ |
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ  ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወመኅ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |
| ወ/ም መስፍን ጌታቸው | ዕሮብ | 4631 N. Beacon St., Chicago, IL 60640 |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናል።

*“እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀብለን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናልና ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና፤ ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ።” (ዮሐ. 1፡ 16-17)*

በመካከላችን ሲያገለግለን የቆየው ወንድማችን ፓ/ር (ዶ/ር) ኃይሉ ቸርነት በአመት በዓል ሰሞን የሚያስታውሰን አንድ ቁም-ነገር ነበር። “እኛ አበሻ ክርስቲያኖች ድርብ ምጻተኞች ነን” ይላል። አባባሉን የሚጠቀምበት እንደ ክርስቲያኖች በምድር ስንኖር ምጻተኞች እንደሆንን ሁሉ ላለንበት አገርም እንግዳ መሆናችችን ለማመልከት ነው። ፓ/ር ኃይሉ በዓላትንም አስመልክቶ ሲናገር “እኛ አበሾች እድለኞች ነን ምክንያቱም ድርብ በዓል እናከብራለንና” ይላል። እነሆ አሁንም የፈረንጆቹን ገና አክብረን ዛሬ ደግሞ የአበሻውን ገና እናከብራለን። ለነገሩ ለኛ ገና (የጌታ ልደት) የየለቱ በአላችን ነው። በድጋሚ እንኳን ለብረሃነ ልደቱ አደረሳችሁ!

ሰዎች በገና ሰሞን ብዙ ስጦታ ይለዋወጣሉ። ገና የስጦታ በዓልም ተደርጎ ይወሰዳል። አሁን አሁን ንግድ በዛበት እንጂ የሃሳቡ መሰረት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። ገና አብ የከበረውን ስጦታውን -- የሚወደውን አንድ ልጁን — ለአለም ሁሉ የሰጠበትን እለት በማሰብ የምናከብረው በዓል ነው። እግዚአብሔር ለምን አንድ ልጁን ሰጠን ብለን ስንጠይቅ መልሱ ስለሚወደን ነው። ዮሐንስ በወንጌል እንደ ጻፈልን “በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።” (ዮሐ. 3፡16) ልጁን ሲሰጠን በልጁ አምነን ሕይወት እንዲሆንልን ነው። በልጁ አምነን የእግዚአብሔር ሕይወት ተካፋዮች ስንሆን ደግሞ ወደ ተትረፈረፈ የጸጋ ሙላት ውስጥ እንገባለን። ለዚህም ነው መጽሐፍ በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናል የሚለን።

ጌታ ኢየሱስ ሲወለድ (መለኮት ስጋ ሲሆን) ጸጋና እውነትን ተሞልቶ ነው በመካከላችን ያደረው። እኛም በእምነት ከዚም ሙላት ተካፋዮች ሆንን። ከሙላቱ ተቀበልን። በመጀመሪያ የሕይወትን ስጦታ ተቀበልን። መጽሐፉ “በእርሱ ሕይወት ነበረች፥ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች” ይለናል። (ዮሐ. 1፡4) ጌታ ኢየሱስ የመጣው ይህንን በርሱ ያለውን መለኮታዊ ሕይወት ሊያካፍለን ነው። ስለዚም በቃሉ “እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ” ይለናል። (ዮሐ. 10፡10) በርሱ ያገኘነው ሕይወት የሚበዛና የተትረፈረፈ ሕይወት ነው። (“ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ <u>ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን</u>።” ኤፌ. 2፡5) የተሰጠን ትልቁ ስጦታ ሕይወት ነው። ምክንያቱም ለሙት የሚያስፈልገው ፈውስ ሳይሆን ሕይወት ነውና። ይህ በክርስቶስ ያገኘነው ሕይወት ጨለማን ሁሉ የሚገፍ ብረሃንም ነው። የተቀበልነው የሕይወት ብርሃን በጨለማ ላይ ይበራል። ጨላማም አያሸንፈውም።

ከክርስቶስ ጋር የእግዚአብሔርን ሕይወት በመካፈላችን ደግም የእግዚአብሔር ልጅነት ማእረግ አገኘን። ዮሐንስ ይህንን ሲያበስረን “የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። <u>ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው</u>” ይለናል። (የሐ. 1፡11-12) ልጆች በመሆናችን መንፈሱ ተሰጠን። (ሮሜ. 8፡15) በውስጣችን ያለው መንፈስ የሚረዳና የሚያበረታ፣ ልጅነታችንንም የሚመሰክር መንፈስ ነው። ልጆችም በመሆናች ደግሞ እግዚአብሔርን የምንወርስ ማለትም የመልኮትን ባህርይ የምንካፈል ሆነናል። ኢየሱስ ጸጋና እውነትን ተሞልቶ በመካከላችን መጣ። እኛ በርሱ በማመን በጸጋ ላይ ጸጋ ተቀበልን። አሁንም በእምነት ወደ ጸጋው ዙፋን ስንቀርብ ሌላ ጸጋ እንቀበላለን። ክብር ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሁን። መልካም የገና በዓል ይሁንልን!